# ★ ዴሞክራሲያ ★

ዴሞክራሲያ ቅፅ 40 ቁ. 6 — መጋቢት 2007 ዓ.ም


# ስለ ሴቶች ትግል ስናወሳ

በ1995 ዓ.ም በቻይና ዋና ከተማ በፔኪንግ የተሰበሰበው 4ኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ጉባዔ ውይይቱን አካሂዶ በደረሰበት ውሳኔ መሠረት "የሴቶች ትግል ለሰብዓዊ መብት ነው“ የሚለውን የመቀስቀሻና የማታገያ መሪ ቃል ለዓለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ኃይል ማሰማቱ የሚታወስ ነው። በርግጥም የዚህን መርህ ውስጣዊ ይዘት በጥልቀት ለሚያጤነውና እንዲሁም ለማንኛውም ለሴቶች መብት ቀናኢ ለሆነ ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ ግልጽ ሊሆን የሚችለው ጉዳዩ መሠረታዊ ክብደት ያለው መሆኑና የሚደፋው ሚዛንና እየተሰጠው ያለውም ግምት ቅንጣትም ታህል ያልቀነሰ መሆኑን ነው።

የዚህ ምክንያት ልዩ ምስጢር አይደለም። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሴቶች በተለይም ወጣት ሴቶች ሰብዓዊነትና ክቡርነትን የተላበሰ የኑሮ ሁናቴ አልተጎናጸፉም። ለኑሯቸው አስፈላጊ የሆኑትን ማለትም የንፁህ ውኃ አቅርቦት፤ ለጤንነትና ለእዕምሮ መዳበር ተስማሚ የሆኑ የምግብ አይነቶች፣ ተገቢ መጠለያና አልባሳት አያገኙም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሀገሪቷ የምታፈራውን ሀብት እንደሚያበረክቱት የሥራ አገልግሎትና ችሎታ መሠረት ዕኩል ተካፋይና ተቋዳሽ የመሆን መብትም የላቸውም። የሴቶች የነፃነት መብት በሁለመናው መልኩ ያለምንም ገደብ እንዲከበር እየታገሉ ያሉ ሴቶች ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ በመሄዱ ምክንያት ነው ጥያቄው አሁንም ከፍተኛ ክብደትና ሚዛን ይዞ የሚገኘው።

ስለ ሴቶች የነፃነት ትግል ሲወሳ ብዙ ጊዜ በብዛት የሚጠቀሰው፣ የአንድ ማንነቱ ያልታወቀ ቻይናዊ በመጀመሪያ ተናገረ የሚባለውና በወቅቱ የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ሊቀመንበር የነበሩት ማኦ ዜዶንግም የቻይና ሴቶችን የኑሮ ሁናቴ ለመግለፅ ሲሉ በሰፊት የተጠቀሙትን "ሴቶች የሰማይን ግማሽ አካል ተሸክመዋል" የሚለው ብሂላዊ አነጋገር ነው። ይህንን የአነጋገር ዘይቤ በአፍሪካ ባጠቃላይ በተለይም በኢትዮጵያ ካለው ሁኔታ አንፃር ስንመለከተው፤ ሴቶች እንዲያውም 3/4ኛውን የኅብረተሰቡን ሸክም የተሸከሙ ናቸው ቢባል ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ በሚገባ የሚገልፅ ይመስለናል። "እንድን ወንድ ሕፃን ልጅ ኮትኩተህ ብታሳድግ የምታፈራው አንድ ግለሰብ ነው፤ አንዷት ሴት ሕፃን ልጅ ብታሳድግ ግን የምታፈራው አንድ ሕብረተሰብ ነው“ የሚለውም አነጋገር የሚያመላክተው ለእናቶችና ወጣት ሴቶች የሚሰጠው እሴትና ግምት ከፍተኛ መሆን እንዳለበት ነው።

ታዲያ ይህ ሆኖ ሳለ እናቶችና ወጣት ሴቶች "የሰማይን ግማሽ አካል ተሸካሚ ናቸው" እየተባለ እየተነገረላቸው፣ ለምንድን ነው በየቀኑ በጣም ለአሳዛኝና ለአሰቃቂ የመብት ጥሰትና በደል ተዳርገው

የሚገኙት? ለምንስ ነው የነፃነት መብታቸውን አለገደብ ተጠቃሚ ሊሆኑ ያልቻሉት? የሚሉት ጥያቄዎች ካለፉት በርካታ ዓመታት አንስቶ አሁንም ድረስ በስፋት የሚያነጋግሩ ሆነው ቀጥለዋል።

ተጨባጩ ሁናቴ እንደሚያመላክተውም በብዙ ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ በሚያሳዝን ሁኔታ ሴቶች በተለይም ወጣት ሴቶች ከፍተኛ ስቃይና በደልን ተሸካሚ ሆነው እናገኛቸዋለን። ማንኛውም ኅብረተሰብ የነቁና የጠነከሩ ጀግና ወጣቶችን በተለይም ወጣት ሴቶችን የሚሻ መሆኑ በተለያዩ ጥናታዊ ምርምሮች የተረጋገጠ ነው። የሴቶች መበደልና መጨቆን በሁለመና መልኩ ባልተወገደበት ሁናቴ ሥርዓቱ አምባገነናዊ፤ የወንድ የበላይነት የሰፈነበትና እንዲሁም የተንሸዋረረ ዴሞክራሲ ከማንፀባረቁም ሌላ ኅብረተሰቡ የተሟላ እድገት ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ጠባብ መሆኑን የሥነ ጥበብ ተመራማሪዎች አበክረው ይገልጻሉ።

ለዚህም ነው የሴቶች መብት በተለይም የነፃነት መብታቸው አለገደብ ይከበር ሕጋዊ ዋስትና ያግኝ የሚለው ጥያቄ ስፋትና ሚዛን ደፍቶ በሰፊው እየተስተጋባ የሚገኘው ። ሴቶች ምንም እንኳ በበርካታ አካባቢዎች የራሳቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን ሆነ የኅብረተሰቡን ቀንበር በመሸከም ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም ጥረታቸው አግባብነት ባለው ሁናቴ አጸፋዊ ከበሬታ አላሰጣቸውም። እንዲያውም በርካታ ጥናቶች እንደሚያረጋግጡት አድሎዎና በበታችነት የመታየት ሁኔታ በግልፅም ሆነ በስውር እየደረሰባቸው ይገኛሉ።

በድህነት፣ በተለይም ደግሞ በየጊዜው እየናረ በሚሄደው የኑሮ ውድነት እየማቀቁ ከሚገኙት መካከል እንዲሁም መሠረታዊ ትምህርት ከተነፈጉት በተለይም የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳያገኙ ከተደረጉ ዜጎች ውስጥ አብዛኛዎቹ ሴቶች ለመሆናቸው የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በየዓመቱ በእርግዝናና በወሊድ ወቅት በሚከሰቱ ጠንቆች ምክንያት ሕይወታቸው የሚያልፈው የሴቶች ቁጥር በርካታ ነው። በወጣት ሴቶች ላይ እየደረሰ ያለው ኃይል የተሞላበት ትንኮሳና በባህልም ተስታኮ የሚደረጉ መብት አፋኝ የሆኑ ተግባራት የሚዘወተሩና በስፋት የሚታዩ ናቸው። አሁንም ድረስ ከፍተኛ የሥራ ሸክምና ጫና በሴቶች ትከሻ ላይ የወደቀ ቢሆንም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሥርተዋል፤ በኤኮኖሚ ዳብረዋል ተብለው በሚጠቀሱት ሀገራት እንኳ ሳይቀር ለሥራቸው ተመጣጣኝ ክፍያ አያገኙም። የነፃነት መብታቸው አለገደብ ስላልተከበረላቸው በፖለቲካውና በኤኮኖሚው መስክም በእኩልነት ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸው መብት በጾታቸውና በተለያዩ ምክንያቶች የተገደበ ነው።

የመንግሥት አካል በሆኑ ሕዝባዊ ምክር ቤቶች፤ የዳኝነትና የአስተዳደሩ ተቋሞች ውስጥ የሴቶች ቁጥር በጣት ከሚቆጠሩ አገራት በስተቀር ለማጌጫ የቀረቡ በሚመስል ሁኔታ አንዳንድ ሴቶች ከመኖራቸው በስተቀር በአግባቡ የሴቶች ተሳትፎ አይታይም። በኤኮኖሚ እድገት ውስጥ ሴቶች የራሳቸውን አስተዋፅዖ ለማበርከትና ያላቸውን እምቅ የችሎታ ኃይል ለማቅረብ ፍላጎትና ዝግጁነት ቢኖራቸውም በበርካታ አካባቢዎች ለሴቶች የሚሰጠው ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ የኅብረተሰቡ እምቅ ኃይል ባክኖ መቅረቱ ብቻ ሳይሆን በኤኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖም በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ሴቶች በሂደት የሚያካብቱት እውቀትና ተመክሮ፤ የሃሳብ አፍላቂነታቸው፤ ንቁ ተሳታፊነታቸው ለማንኛውም ኅብረተሰብ እድገትና ብልፅግና በጣም ወሳኝ መሆኑ በየጊዜው ግንዛቤ እያገኘ ቢመጣም በተግባር እንዳያውሉት ከፍተኛ ጋሬጣ ተደቅኖባቸዋል። የትምህርት፣ የሥራና የንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶም የሚታዩት የመብት መዛነፎች የዚሁ ጋሬጣ ነፀብራቆች ናቸው።

በሌላ በኩል በገሃድ እንደሚታየው የፆታ ልዩነት ከግምት በማይገባበት ኅብረተሰብ ውስጥ ለምሳሌ በምግብ እጦትም ሆነ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሞት የሚዳረጉት ሕፃናት ቁጥራቸው እጅግ በጣም አናሳ ነው። የዚህ ዓይነቱ ኅብረተሰብ ኤኮኖሚው በየጊዜው እያደገ መሄድ ብቻ ሳይሆን የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚና ተሳታፊ የመሆን እድሉ በጣም የሰፋ ነው። ሴቶች እውቀትን የመገብየት፤ ኑሯቸውን በራሳቸው ሙሉ ኃላፊነት ለመምራት እድል ያላቸው ሲሆኑ የቤተሰብ እቅዳቸው በብዙ ሁናቴ መስተካከሉም የሰፋ ነው።

ለዚህም ነው "የፆታ እኩልነት ሰብዓዊ መብት ነው“ ተብሎ አፅንዖት በተሞላበት መልኩ የሚገለፀው። የዚህ መሠረታዊ መብት መከበር የብዙኃኑን የኅብረተሰብ አባላት የኑሮ ሁናቴ ያሻሽላል። ኤኮኖሚያዊ እድገትና ማኅበራዊ ብልፅግናን ያስገኛል። ድህነትንም ሆነ በተለያዩ በሽታዎች የመጠቃትና ለሞት የመዳረጉን ሁኔታ በእጅጉ ይቀንሳል። ከዚህም የተነሳም ዘላቂነት ለሚኖረው የኤኮኖሚ እድገት መሠረት ይጥላል፤ ኅብረተሰቡም የትሩፋቱ ተጋሪ እንደመሆኑ መጠን እንደ ዐይን ብሌኑ ይንከባከበዋል።

የሴቶች መበት አለገደብ አለመከበሩ - ማለትም ጤንነታቸው የሚጠብቅበት ሁኔታ አለመፈጥሩ፤ ትምህርት የማግኘትና ስለራሳቸው የወደፊት ኑሮ በራሳቸው የመወሰን መብታቸው አለመጠበቁ፤ መሠረታዊ ፍላጎታቸውንና ጥቅማቸውን ሊያስከብሩ አለመቻላቸው፤ በሀገሪቱ የወደፊት ዕጣ ተሳትፎ የማድረግና በውሳኔዎችም ተካፋይ እንዲሆኑ አለመቻሉና ሌሎችንም ሙሉ ችሎታቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሏቸው ሁኔታዎች እንዲሟሉላቸው አለመደረጉ - ለመልካም አስተዳደር እጦት፣ ለፍትህ መዛባት፣ ለአድሎ ተግባራት ለሌሎችም ችግሮች ከፉኛ ተጋልጠው ይገኛሉ። ለችግሮቻቸው መፍትኄ ሊሆኑ የሚችሉትን በራሳቸው መንገድ ለመፈለግና ለማግኘት ጥረት እንዳያደርጉ ነፃነታቸውን ተነፍገዋል። ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ በተወሰኑ አካባቢዎችና መስኮች የተወሰኑ መሻሻሎች ቢስተዋሉም በመሠረቱ ከፉኛ ተዛብቶ የሚገኘው የፆታ እኩልነት ሊቀየር አልቻለም። ለዕኩል ሥራ ዕኩል ክፍያና በሁሉም የሙያ መስክ ዕኩል ዕድል አለመኖር ሁለንተናዊ ችገሮች እንደሆኑ ቀጥለዋል። አሁንም ቢሆን በርካታ የሚሆኑ ሴት ሕፃናት የመጀመሪያ ትምህርት ቤትን ለመጎብኘት ከወንዶቹ ሲነጻጸር ያላቸው ዕድል በጣም የጠበበ ነው። ይህንን ዕድል ያገኙ ወጣት ሴቶችም ቢሆኑ በኑሮ ችግርና በሌሎችም ምክንያቶች በወላጆቻቸው ግፊትም ለወንድሞቻቸው ሲሉ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ የሚገደዱ ቁጥራቸው በርካታ ነው።

አካላዊና ስሜታዊ የልዩነት ተግባራት በፆታ ልዩነት ላይ የተመሠረቱ በደሎች ናቸው። ሴቶችን በተለይም ወጣት ሴቶችን ለባርነት መሸጥም ሆነ፣ ለተደበቀ የሴተኛ አዳሪነት የመዳረግ ምንጨ ብልሹ ሥርዓተ ማኅበር፣ አጠያያቂ ከሆነ የሞራልና ከተሳሳተ የጾታ ግንዛቤ የመነጨ በመሆኑ በሴቶች ላይ የሚያሳድረው የበታችነት ስሜት በእጅጉ የከፋ ነው። በሴቶች የሚደርሰው አስገድዶ መድፈርና ጾታዊ ትንኮሳ ከአቻ ወንዶች ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ የበዛ ነው። አሁንም ቢሆን፣ በተለይም በገጠሩ አካባቢ፣ ሴቶችና ወጣት ልጃገረዶች ስለ ግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃፍረትን ሳይላበሱና ጭንቀት ሳይሰማቸው የሚወያዩበት ርዕስ አይደለም። ይህም ስለራሳቸው ግላዊ ፍላጎት፣ በራሳቸው ሙሉ ነፃነትና ጤናማ የሆነ ደስታና እርካታ በተሞላበት ሁኔታ ሕይወትን ለሚቀጥለው ትውልድ በማስተላለፍ ተግባር ላይ እንዳይሰማሩ ወይንም ደግሞ የራሳቸውን አስተዋፅዖ እንዳያበረክቱ እድሉን እንደዘጋባቸው ይገኛል።

ሴት ሕፃናት በጨቅላ እድሜያቸው በሚካሄድባቸው ግርዛት የተነሳም በወደፊት ህይወታቸው ላይ የሚያደርስባቸው የአካልና የሕሊና ቁስል በቀላሉ የሚገመት እንዳልሆነ የሥነ ጥበብ ተመራማሪዎች አበክረው የሚገልፁት ነው። በቤተሰብ ደረጃም ቢሆን የወንድ የበላይነት በነገሰበት ምህዳር ለመኖር በመገደዳቸው ምክንያትም፤ ጤንነታቸውን የጠበቀ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የማድረግ መብታቸው አይከበርላቸውም። በዚህም የተነሳ ሕይወት ቀሳፊ ከሆነው ኤች.አይ.ቪ. አንስቶ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጡ ናቸው። ያለ ፍላጎታቸውና ያለ እድሜያቸው በጨቅላነታቸው በወላጅ አስገዳጅነት ለትዳር፣ ለኤኮኖሚና ማኅበረሰባዊ ብዝበዛ፤ ለርካሽ የሥራ ኃይል ተጋላጭ የሚሆኑ ባብዛኛው ሴት ሕጻናቶች ናቸው። ለአቅመ ሄዋን ሳይደርሱና ልጅነታቸውን በሚገባ ሳያጣጥሙ ለትዳር ተዳርገው ያለዕድሜያቸው በሚከሰት እርግዝናና ወሊድ ምክንያት ሕይወታቸው ባጭር የሚቀረው፤ ዕድሜያቸውን ሙሉ በሚያሰቃይ የፌስቱላ ሕመም የሚጋለጡ እህቶቻችን ቁጥር ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ። ይህ ሁኔታ በተለይ እድሜያቸው ከ 20 አመት በላይ ከሆኑት ሴቶችና ለሞት ከሚዳረጉት ጋር ሲነፃፀር እጥፍ ድርብ እንደሆነም በዚህ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ተለምዶ፣ ባሕልና የሥነልቦና ግንዛቤም በሴቶችና ወጣት ልጃገረዶች ላይ ለጾታ ልዩነት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። በሴቶች ላይ እየተፈፀመ የሚገኘው የአድልዎ ተግባር፣ በአካባቢና ብሎም በሀገር አቀፍ ካለ ባሕላዊ አመለካከት፤ እንዲሁም ከተለምዶና በሂደት ከሚገኝ ግንዛቤ ጋር የተያያዘ ነው። እንደዚሁም የእምነት አስተሳሰቦች የወንዶችን የበላይነት፣ የሴቶችን የበታችነት ስሜት የሚያንፀባርቁ ናቸው። ይህ እይታ በሥርዓተ ማኅበሩም ቦታ እንዲኖረው በመደረጉ የፆታ ልዩነት በዘላቂነት እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አርጓል።

የሴቶች መብት እንዲከበር በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ አንቀፆች ሕገ መንግሥታቸው ውስጥ ቢካተቱም በአሁኑ ወቅት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመሠረቱ ሀገራት እንኳ ሴት ነክ የሆኑ መብቶች እንደ ቀላልና የተለመደ ተደርገው ቢታዩም፤ ለዚህ መብት መከበር ሲሉ በርካታ ሴቶች እልህ አስጨራሽ ትግል አካሂደው ከፍተኛ መስዋዕት የከፈሉበት መሆኑን የሚያስታውሱ ግን ጥቂቶች መሆናቸውን ጥናቶች ይጠቁማሉ። ለዚህም ነው ይህ ከጥቂት ዓመታት በፊት መቶኛ ዓመቱ የተከበረውና አሁንም ድረስ በየዓመቱ የሚዘከረው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ከፍተኛ ቦታውና ተገቢ ክብሩ በሁሉም ዜጎች ሕሊና ሰርፆ እንዲገባ ከሚያበረክታቸው አስተዋፅዖ መካከል አንዱ ተደርጎ በስፋት እየተገለፀ የሚገኘው። ይህ ቀን ሴቶች በተናጠልም ሆነ ከሌሎች ዴሞክራሲያዊ ኃይላት ጋር በጋራ ታግለው ማስከበር ያለባቸውን የመብትና የእኩልነት ጥያቄዎች የበለጠ እንዲስተጋቡ የሚያደርጉበትና፣ የወደፊቱን ትግላቸውን አቅጣጫ የሚያሲዙበት በመሆኑ በመላው ዓለም በድምቀት ተከብሮ ሊውል ይገባዋል። በሀገራችን በወያኔ አገዛዝ ግን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል ቅንነትና ቁርጠኝነት በጎደለው መልኩ ቀኑ መታወሱን በአግርሞት የምንታዘበው ነው - ሀገራችን በወያኔ፣ የመላው ዜጋ ምንም ዓይነት መብት የማይከበርባት አገር መሆኗንም ልብ ይሏል።

ኢሕአፓ ጤናማ ለሆነ የዜጎች ግንኙነት፤ በሰላማዊ ኑሮ ላይ ለሚመሠረት ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ እድገት የሴቶች ጥያቄ በተገቢው ሁናቴ መፍትኄ ሊሰጠው ይገባል የሚል የጸና እምነት አለው። ይህንንም በተደጋጋሚ የገለፀውና ለተግባራዊነቱም አበክሮ የሠራበትና ወደፊትም የሚሠራበት ነው። በዚህም ምክንያት ነው፣ ሴቶች የነፃነት መብታቸውን ባልተጎናፀፉበት ሁኔታ ጤናማ የፖለቲካ ሥርዓት ሰፍኗል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም ሲል ሳያሰልስ የሚገልፀው። ከማኅበረሰባችን ውስጥ ከግማሽ ቁጥር በላይ የሆኑት ሴቶች ጥያቄያቸው፣ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በርግጠኝነት መብታቸው ሳይከበርላቸው፣ እኩልነታቸው በቃል ሳይሆን በገቢር ሳይረጋገጥላቸው፣ በሀገራቸውና በራሳቸው መብት ዙሪያ ሙሉ ተሳትፎ ሳይኖራቸው የችግሮቻቸው የመፍትኄ አካል ሊሆኑ አይቻላቸውም። የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል በመሆናቸውም ሕብረተሰቡ ራሱ ባጠቃላይ ነፃነቱን ሳይጎናፀፍ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሳይመሠረት ሴቶችም የነፃነት ካባ ሊላበሱ እንደማይችሉ ግልፅ ነው - ግማሽ ነፃነት የለምና!

ለዚህም ነው ኢሕአፓ ገና ከጥንሥሱ የጥናት ክበብና የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ በማደራጀትና በማበረታታት የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማበርከት በስፋት መንቀሳቀስ የጀመረው። የሴቶች ጥያቄ ራሱን የቻለ ግን መላ ሕብረተሰቡን የሚመለከት ጥያቄ መሆኑን በሚገባ በመገንዘብ፤ ሴቶች ለትግሉ በተማሪው እንቅስቃሴም ሆነ በኋላም በኢሕአፓ ውስጥ ተሰልፈው ለራሳቸው፣ ብሎም ለጠቅላላው ሕብረተሰብ ነፃነትና መብት መከበር እንዲታገሉ ከፍተኛ ቅስቀሳ በማካሄድ የራሱን አስተዋጽኦ አርጓል። በዚህም የተነሳ በየካቲቱ ሕዝባዊ አመፅ ሴቶች ግንባር ቀደም በመሆን የአፄውንም ሆነ ቀጥሎም የደርግን አገዛዝ ታግለዋል። የደመቀ ታሪክን በደማቸው አቅልመው ፅፈዋል። በኢሕአፓም ተደራጅተው በገጠርና በከተማም አኩሪ የሆነና በአርዓያነት የሚታይ ገድል ሠርተው ያለፉ ቁጥራቸው በርካታ ነው።

ቀደም ብሎም ቢሆን በርካታ እናቶቻችን የሀገር ሉዓላዊነትና ነፃነት መከበር የወንድ ማንአህሎኝነትና የበላይነት ሳይበግራቸው ከከፍተኛ እርከን አንስቶ በተለያዩ ደረጃዎች አመራር በመስጠት ከታጋይ ወንድሞቻቸው ጎን በመሰለፍ መሣሪያ አንስተው ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ለሀገራቸው፣ በጀግንነት መስዋዕት

ሆነው አልፈዋል። ይህ የከፈሉት መስዋዕት በሕዝባችን ታሪክ ውስጥ ምንጊዜም የሚታወስ ከፍተኛ ገድል ነው። ዛሬ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ አንገቱን ቀና አድርጎ ሳይሸማቀቅ ኢትዮጵያዊነቱን እየገለፀ የሚገኘው በሴቶች ከፍተኛ መስዋዕት በተገኘ ድል ጭምር እንደሆነ ሙሉ እምነታችን ነው። የሴቶች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የኢሕአፓ የትግሉ አልፋና ኦሜጋ ሆኖ የሚገኘውም በዚሁ ምክንያት እንጂ በሌላ አይደለም።

ለዚህም ነው የወያኔ አገዛዝ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ቁርጠኛ እርምጃዎች ስለመውሰዱ ለመስማት እስከሚሰለች ድረስ ደጋግሞ ቢገልፅም የፖለቲካ ጠቀሜታ ያስገኝልናል በማለት ከሚያምኑት ጥቂት አጃቢዎቹ በስተቀር ለብዙሃኑ ሴቶች የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳን ክብደት የሌለው መሆኑን በዕለት ተለት መብት አልባ ኑሮ የሚያረጋግጡት ነው። አሁንም ድረስ ወንድ ልጅ ወልዶ ማሳደግ ኢጋዥና አጋር ማግኘት በሚል የተሳሳተ ግንዛቤ፤ ሴት ልጅ መመኘት በወንዶቹ ባጠቃላይ የማያስደስት ምኞት መሆን በተለይም በገጠሩ አካባቢ የተስፋፋ ነው። ለግርድና የተቀጠሩ አስገድዶ የመድፈር ጥቃት ሰለባ የሚሆኑት ወጣት ሴቶች በርካታ ቢሆኑም ባለባቸው የኑሮ ችግር የተነሳ አማራጭም በማጣትና በአነሳሽነት (ሁኔታውን የሚገፉፉ ተብለው) ላለመፈረጅ ሲሉ ተበድለውም ዝምታን የሚመርጡትን ቤት ይቁጠራቸው ማለቱ ምናልባት ይቀል ይሆናል። ለድብደባና ለአካል ጉዳት ለመሳሰሉ የኃይል ጥቃቶች የሚዳረጉት ሴቶች መሪር ሀዘናቸው ለነሱ ብቻ ሳይሆን ለቅርብ ዘመዶቻቸው የመንፈስ ስቃይን እያተረፈና ማኅበራዊ ኑሮን እያናጋ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ሴቶች ለበርካታ ዘመናት ከሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መነፈግ ጋር በፆታቸው ምክንያት እየደረሰባቸው ያለው ድርብ በደልና ጭቆና ተገልፆ የማያልቅ ሰቆቃ ነው። ሁኔታው ገጥሞላቸው ዘመናዊ ትምህርት የቀመሱ ቁጥራቸው አናሳ የሆኑ ሴቶች እንኳ ሳይቀሩ ቤተሰብ ሲመሰርቱ ለትዳራቸው መኅልበት የራሳቸው ገቢ የሌላቸው በመሆናቸው የበላይና የበታች ብሎም የጥገኝነት ስሜት የሚያሳድርባቸው ብቻ ሳይሆን በመካከላቸው ለሚኖር አለመግባባትም የራሱ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ የሚታይ ነው። የወሊድ ክትትል ለማድረግም ቢሆን እየተስፋፋ ባለው ድህነትና የገንዘብ አቅም ማጣት፤ በአቅራቢያቸው በስፋት የሕክምና ተቋማት ያለመኖር ለእናቶችና ለሕፃናት ሕይወት መቀጠፍ በዋናነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች ውስጥ ናቸው።

በኢትዮጵያችን የወያኔ አገዛዝ እንደሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን፣ ሕጋዊና ተቋማዊ አሠራሮች ሴቶችን አሁንም ለጥቃት ከመጋለጥ አላዳናቸውም። በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታና በሌሎችም ሕዝባዊ ቦታዎች ሴቶች ላይ በወንዶች የሚፈፀሙ ጾታዊና አካላዊ ጉዳቶች በርካታ ናቸው። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ወንድን ሳይሆን ሴትን በውበቷ ወይም በአለባበሷ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው አሳፋሪ ምክንያታዊ ገለፃዎች ናቸው። ለመንገድ አዳሪነትና ለወሲብ ባርነት፤ በአደንዛዥ ዕጾች ሱስ መውደቅ (መጠመድ)፤ ለወንዶች ብዝበዛና ዋልጌነት መዳረግ፤ ለድብደባና ጨካኝ ቅጣት ጭምር መጋለጥ፤ ቀኑን እየጠበቀ በሚመጣው ረሃብና ችግር በብዛት ሰለባ እየሆኑ ያሉ በርካታዎቹ ሴቶችና ሕፃናት ናቸው።

ብልሹ የሆነው ሥርዓት በቀጥታና በተዘዋዋሪ በሚያራምዳቸው መድረኮችና ሥዕላዊ ኪነቶቹ ሴቶችን አሳንሰው የሚያቀርቡና ለጥቃትም የሚያጋልጡ መሆናቸው በግልጽ ይታያል፡፡ ድህነትን ለመሸሽ በወያኔ አገዛዝ ዋና አቀናባሪነት ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ለዘመናዊ ባርነት ተዳርገው ለስቃይና ለሞት የተጋለጡ ሴቶች ዜጎቻችን እጅግ በርካታ ናቸው። በተለይ በነዚህ አረብ አገሮች ባለ ከጭለማው ዘመን ፈቀቅ ያላለ የፆታ ጭቆናና ዘረኝነት ምክንያት ከሚደርስባቸው ሰቆቃ ለማምለጥ ባለመቻላቸው ራሳቸውን የሚያጠፉ ወጣት ሴቶች ቁጥር ብዙ ነው። ይባስ ብሎም በቅርቡ የሀገሪቱ ዋና ከተማ አዲስ አበባ የወሲብ ማዕከል በሚል ተቀፅላ መጠራቷ፣ በሥራ አጥነትና በኑሮ ውድነት መናር እየተገደዱ በለጋ እድሜያቸው ለሴተኛ አዳሪነት የተዳረጉት ቁጥር እጅግ በርካታ በመሆኑ ነው። ታዲያ የሴቶች ሁናቴ በሀገራችን ባጭሩ ይህን ሲመስል፤ የወያኔ አገዛዝ የሴቶችን እኩልነት በተግባር የሚያረጋግጥ በሕገ አገዛዙ አስፍሬያለሁ እያለ

መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም፤ ከ23 ዓመታት በኋላም ያለው ተጨባጭ ሁኔታ የሚያሳየው የሙብት መከበርን ሳይሆን በበለጠ መገፈፍን፤ ከድህነት መላቀቅን ሳይሆን ይበልጥ መቀመቅ የወረደ ድህነትን ነው።

ዛሬ ስለ ሴቶች ትግል ስናወሳ ለሴቶች ሙብት መከበር ሲታገሉ መስዋዕት የከፈሉትን በርካታ እህቶቻችንና አናቶቻችንን በሕሊናችን እያስታወስን፤ ለእስር የተዳረጉትን ደግሞ ፅናቱን እንዲሰጣቸው ብቻ ሳይሆን ከእስር ተፈትተው ከዘመዶቻቸው በሰላም እንዲገናኙ የይፈቱ ጥሪ በማቅረብ ነው። ከ1993 ዓ.ም ጀምሮ መዳረሻዋ ያልታወቀው እውቋ የኢሕአፓ ታጋይ አበራሽ በርታና እንዲሁም የቀይ ሽብር ሰለባ ለሆኑት እንደነ አፀደ ወይን፣ ገነት ክፈለው፣ ምርአት አሰገድ፣ አበበች ካሳ፣ አልማዝ ጠፉ፣ ግርሚት ዓለም ደገፉና ሌሎቹም የዚሁ አገዛዝ ሰለባ የሆኑት እልፍ አዕላፎችን ምንጊዜም ከሕሊናችን የማይጠፉ በልባችን ሐውልት የሰራልናቸው ናቸው። እንዲሁም በልባችን ሐውልታቸውን ያቆምንላቸውን፣ የፋሽስቱን ደርግ መንግሥትና ወያኔን ሲታገሉ በዱር በገደሉ መስዋዕት የሆኑትን ጓዲቶቻችንን ዛሬም እንዘክራቸዋለን።

በሀገራችን የወያኔ አገዛዝ ስለ ሴቶች እኩልነት ያልተፃፈ፣ ያልተወራ፣ ያልተለፈለፈ ፕሮፓጋንዳ የለም። በፕሮፓጋንዳ ብዛት ግን የሚሻሻል ሁኔታ ወይንም የሚገኝ ለውጥ ጨርሶ አልታየም። ሕብረተሰቡም ሆነ ሴቶች የነፃነት ሙብታቸውን ስላልተጎናፀፉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ ሙብታቸው ገና አልተከበረላቸውም። በጣት የሚቆጠሩ የአገዛዙ አባላት የሆኑ ሴቶች ምንም ዓይነት የአመራርና የውሳኔ ሰጪነት ሚና በሌላቸው ምክር ቤቶቻቸው ስለተቀመጡ ብዙሃኑ ሴቶች ከመድረኩ ተገለውና ተጨቁነው መገኘታቸውን አይሸፍነውም። ከከፋ ድህነት ለመገላገል የሚያስችላቸው የፖለቲካ ሥርዓትና ምህዳር ገና አላገኙም። ነፃነትና እኩልነት የውሃ ሽታ ናቸው ቢባሉ ሃቁን የሚገልፁ ናቸው።

በወያኔ ሥር ሀገራችን ምንም ዓይነት ሙብት የተከበረባት ባለመሆኗ፣ ሴቶች ዜጎቻችን መሠረታዊ ሙብታቸው በገቢር እንዲረጋገጥ በቀጣይነት ሴቶችን መቀስቀስ፣ እየቀሰቀሱም ማደራጀት፣ እየተደራጁም መታገል አስፈላጊ መሆኑን ማስመር እንፈልጋለን። በማህበረሰቡ ዘንድ ሥር ሰዶ የዘለቀው ሴቶችን ከወንዶች ጋር እኩል ያለማየት የፆታ እኩልነትን ለማስፈን እንቅፋት ሆኖ እንዲቀጥል የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱ በተራ ፕሮፓጋንዳ የሚወገድ እንዳልሆነ ያለፉት 24 አመታት የሚያመላክቱት ነው። በተለይ ወያኔን መሰል ከፋፋይና አረመኔ አገዛዝ የፆታ ልዩነትንም እንዲሁ የሚያራግብ በመሆኑ ልዩነቱ እየሰፋ፣ እንጅ እየጠበበ አልሄደም። ችግሩ ስር የሰደደ እንደመሆኑ መጠን ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት የሚቀረፍም አይደለም። ባጠቃላይ በሀገሪቷ የዜጎች ሙብት መከበርን፤ መላ ዜጋው በቁርጠኝነት ከሴቶቹ ጎን ቆሞ መታገልን፤  ሴቶች እራሳቸው የሚቀጣጠሩት የሴቶች ድርጅት መኖርን ይጠይቃል። ስለሆነም የሴቶች ጉዳይ በቅጡ ይመለከተኛል የሚል ሀገር ወዳድ ዜጋ ሁሉ የትግላቸው አጋር መሆን ሀገራዊ ኃላፊነትና ግዴታ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለን።

ኢሕአፓ የሴቶች ሙብት ያለገደብ ይከበር ሲል ለተራ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን ከልቡ የሚያምንበት ለመሆኑ በአባልነት ተሰልፈው ለሴቶች ሙብት ሲታገሉ የተሰዉ፣ የቆሰሉ፣ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሁሉና አሁንም በአባልነት ግዳጃቸውን እየተወጡ የሚገኙ የሴት አባላቱ ምስክር ናቸው። ዴሞክራሲያ በዚህ መልዕክቷ ልባዊ አድናቆቷንና አክብሮቷን ታስተላልፋለች። የክብር ምስጋናም ትለግሳቸዋለች። በመንፈስም ሁሌም ቀይ እቅፍ አበባ ታበረክትላቸዋለች። ያለ ሴቶች ደማቅ ተሳትፎ ትግላችን አይሰምርምና፣ ለእንቅስቃሴያቸው ያለንን አጋርነትና ለጋራ ትግላችን የድል ጉዳና በአዲስ መልክ እንዲከፍት ያለንን ልባዊ ምኞት ስንገልፅ በኩራት ነው።

የሴቶች ሙብት የማይከበርበት ሥርዓት አምባገነናዊ ነው!!

ድል ለሴቶች ትግል!